*ድራማው የተደረሰው በሙሳንግዋ ኤድዋርድ በሉጉፉ የስደተኞች ካምፕ ሲሆን አላማውም ለትምህርት ነው። ድራሲው ከ CELA እና ከ WTE እንዲሁም ለትርጉም ከሎጋን ኮቻርን ጋር ትብብር አድርጓል።*

**ርዕስ** *"መድሃኒት ሲበዛ ፈውስ አይገኝም"*

**ካምፕ ውስጥ ወንዶች ብዙ ጊዜ በወሲብ ፍላጎት ይጠቃሉ ምንም እንኳ በትዳር ውስጥ ቢሆኑ ። ይህ ድራማ 3 ክፍሎች እና 2 ገጸባህሪዎች አሉት ። ሎጋን እና ኤድዋርድ በወንድላጤነት ለብዙ ጊዜ ኖሮዋል ግን አሁን በጋብቻ እራሳቸውን ሊወስኑ ነው።**

**ክፍል 1**

*<u>ኤድዋርድ</u>: አንድ ሚስጥር በውስጤ ይዣለሁ ነገርግን ልንገረው አልንገረው እያልኩ ከራሴ ጋር እየተከራከርኩ ነው።*
*<u>ሎጋን፡ </u>ጓዴ፡ ከእኔ ጋር ግልጽ መሆን አለብህ*
*<u>ኤድዋርድ፡ </u>እሺ ስማኝ። የወንደላጤነት ህይወታችንን ብንቀይር ደስ ይለኛል። ስለ ጋብቻ ማሰብ ጀምሪያለሁ።*
*<u>ሎጋን፡ </u>ጥሩ ሃሳብ ነው። በእርግጥ እንደዚህ አይነት ውብ የሆነ ሃሳብ ከአፍህ ወጥቶም አያውቅ። በአሁኑ ጊዜ ኤች.አይ. ቪ/ኤድስ ትልቅ አደጋ ላይ ስለሚጥለን ከህጋዊ ሚስቶቻችን ጋር ብቻ ነው ወሲብ መፈጸም ያለብን። ነገር ግን ጋብቻ ማለት አንድ ለአንድ ለአንድ መወሰን እንደሆነ መገንዘብ አለብን። ደግሞም መጽሐፍ ቅዱስ የሚያዘውም ይሄንን ነው።*
*<u>ኤድዋርድ፡ </u>ሎጋን ብዙ አትጨነቅ። አንድ ለአንድ መወሰን አያቅተንም።*

**ክፍል 2፡ ሁለቱም ጋብቻ መስረቱ።**

*ለሁለት አመታት ሎጋን እና ኤድዋርድ ከሚስቶቻችው ጋር በቅንነት ሲኖሩ ቆይተው ከጊዜ በኋላ ግን ኤድዋርድ ሚስቱን መክዳት ጀመረ። ወጣት በመሆኑ አንድ ለአንድ መወሰን ከባድ መሰለው እንዲሁም ሚስቱን እንደ "ፉራ" ማየት ጀመረ።*

*<u>ኤድዋርድ፡ </u>ሎጋን እኔ በአሁኑ ጊዜ ከወጣት እና ትኩስ ከሆኑ ሴቶች ጋር ነው ያለሁት። ካለእነሱ እርካታ ማግኘት አልችልም።*
*<u>ሎጋን፡ </u>እንዴ! ምን ማለትህ ነው?*
*<u>ኤድዋርድ፡ </u>ግልጽ አድርጌ የነገርኩህ መሰለኝ። ከሚስቴ እርካታ ማግኘት አልቻልኩም። ስለዚህ ከሌሎች ወጣት ሴቶች ጋር መዝናናትን ተያይዤዋለሁ።*
*<u>ሎጋን፡ </u>አብረሃቸው የምትተኛው ሴተኛ አዳሪዎች በኤድስ የተጠቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ከእነኡ የምታመጣው በሽታ ለቤተሰቦችህ እንዳይተርፍ። በተለይ ደግሞ ለህጻናቶቹ።*
*<u>ኤድዋርድ፡ </u>እንደዚህ እያልክ አታስፈራራኝ። የምትላቸው ነገሮች ሁሉ አፈ.ታሪክ ናቸው። በግዜዬ መደሰት እፈልጋለሁ።*
*<u>ሎጋን፡ </u>እባክህን ተለመነኝ። ህይወትህን በገዛ እጅህ አታሳጥር። ለልጆችህ እንኳን እስቲ ኑርላችው። እኔም ያለአንተ ጓደኛ የለኝም። ለምን ራስህን አትቆጣጠርም?*
*<u>ኤድዋርድ፡ </u>ባክህ ተወኝ። አትጨቅጭቀኝ። ጓደኛዬም ብትሆን ይህ የኔ ህይወት እንጂ ያንተ አይደለም።*
*<u>ሎጋን፡</u> አዝናለሁ።*

ክፍል 3፡

*“ያልተጠበቀ ክስተት”፡= ለሁለት አመታት ያህል ኤድዋርድ ከሴተኛ አዳረዎች ጋር ሲተኛ ቆይቶ መጨረሻ ላይ በኤች. አይ. ቪ. ተጠቃ። በእርሱ ምክንያት ሚስቱ እና ልጆቹም ተጠቁ። ልጆቹ ለህልፈተ ህይወት ተጋልጠው አሁን ሁለት ብቻ ናቸው የቀሩት።*

ኤድዋርድ፡ ሎጋን፤ ከሞት አፍአፍ ላይ ነው ያለሁት። ሁለቱን ልጆቼን አደራ።

ምክር፡ ከዚህ አንድ ትምህርት ልንማር እንችላለን። የድራማው ርእስ “መድሃኒት(ወሲብ) ሲበዛ ፈውስ አይገኝም” የሚል ነበር። አንድ ለአንድ መወሰን እና ለትዳር ጓደኞቻችን ታማኝ መሆን ልጆቻችንን ከወላጅ አልባነት ያድናል። ሀገራችንንም ከድህነት ይጠብቃል።

